# ምድብ ሦስት (ከ4ኛ — 6ኛ) ክፍል

## 24 ኛ ሳምንት

## መክሊት

**የትምህርቱ ዓላማ**

- የተሰጠን በአግባቡ ስለመጠቀም መማር።

**የሚጠና ጥቅስ**

- *"አንተ ታማኝ ባርያ በጥቂት ታምነሀል በብዙ እሾምሃለሁ።"* ማቴ 25÷21

**ምንባብ**

- ማቴ. 25÷14-30

**መግቢያ**

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረዘይት ምሳሌዎችን እየሠጠ ብዙ ትምህርቶችን አስተምሮአል። በማቴ. 25÷1 - ፍጻሜ ምዕራፍ በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሱት ምሳሌዎችም የሚከተሉት ናቸው።

  1. ስለ10ሩ ደናግል 2. ሦስቱ ባለመክሊቶችና 3. የበግና የፍየል ምሳሌ ናቸው።

- በዛሬው ትምህርታችንም መክሊትን ስለማትረፍ ጌታችን ያስተማረውን እናያለን።
- 6ኛው የዐቢይ ጾም ሳምንትም በዚህ የመክሊት ምሳሌ በተመሰገነው ታማኝ አገልጋይ - ገብርኄር ተብሎ ተሰይሞአል።

**የክለሳ ጥያቄዎች**

1. በቀኝ ላሉት ምን ይላቸዋል በግራ ላሉትስ?
2. በጌታ ቀኝ ለመቆም ምን ማድረግ አለብን? ከመምህር ጋር ተወያዩ

**የትምህርቱ ዋና ይዘት**

- ጌታችን ባሮቹ እንደየአቅማቸው መክሊት ሰጥቶ ስለሄደ ባለጣጋ ምሳሌን ሰጥቶ እንዲህ አስተማረ፡-
- ወደ ሌላ አገር የሚሄድ እንድባለጠጋ ሰው ሦስት ባሮቹን ጠርቶ ለእያንዳንዱ እንደየአቅሙ ሠጣቸው ለአንዱ አምስት ለሌላው ሁለት ለሦስተኛውም አንድ መክሊት ሠጠና ሄደ።
- ባለ አምስቱ ሄዶ ነገደበትና አሥር መክሊት አድረገው።ባለ ሁለቱም እንዲሁ አትርፎ አራት አደረገው።ባለ አንዱ ግን መሬት ቆፍሮ ደበቀው።
- ከብዙ ዘመንም በኋላ የነዚያ ባሮች ጌታ መጥቶ ተቆጣጠራቸው እያስጠራም ገንዘቡን ምን እንዳደረጉበት ጠየቃቸው።ባለ አምስት እና ባለ ሁለቱ ማትረፋቸውን ሲገልጹ ባለ አንዱ ግን በጌታው አማካኝነት ፈርቶ እንዳለተረፈበት ነገሮ ከቆፈረበት አውጥቶ መለሰለት።
- ያ ባለጠጋም መክሊታቸውን ያተረፉትን አንድ ባንድ *"መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂት ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ።"* አላቸው። የቀበረውንም *"አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ……… ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሠጠው በተገባህ ነበር÷ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር"* አለው።ወደ ውጪ አውጥተው እንዲጥሉትና ያለውን ለሌላ እንዲ ሠጡበትም አዘዘ።

  **ከዚህ ምሳሌ የሚከተሉትን እንማራለን፡-**

1. **እግዚአብሔር የሠጠንን በአግባቡ መጠቀም አለብን።** ሁለቱ ባሮች የተሰጣቸውን በአግባቡ ስለ ተጠቀሙ በሚበልጠው ተሹመዋል። እኛም እግዚአብሔር በሠጠን ትምህርት፣ቤተሰባዊ እንክብካቤ፣አዕምሮ እና ተሰጥዖ ተጠቅመን በአግባቡ ካጠናን፣ቤተባችንን ከታዘዝን እና በተሰጠን ማስተዋልና እውቀት በአግባቡ ከተጠቀምን፡-

   እግዚአብሔር ይባክናል። የበለጠ እውቀትና እድሜ ይሠጠናል።ቤተሰቦቻችንም ውጤታችንን አይተው የተሻለ ነገር ያዘጋጁልናል። ይደሰቱብናል።ይመርቁናልም።

2. **ስንፍናን ማስወገድ።** ወደ ውጭ የተጣለው ሰው ሰነፍ ነበር። እኛም እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንና ቤተሰቦቻችን እንዳያዝኑብን በትምህርት፣ በምንታዘዘውም ፈጣንና ጎበዝ በመሆን ሰውና እግዚአብሔርን ማስደሰት አለብን።

**ተግባር፡-**

1. በቤተክርስቲያን የተማራችሁትን ፈጽሙ
2. በትምህርታችሁ የተሻለና ውጤታማ ለመሆን ሁሌም ንቁና በእግዚአብሔር እገዛ የምትተማመኑ ሁኑ
3. ስለትምህርቱ ከመምህር ከቤተሰብና ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ።

**ጥያቄዎች፡-**

1. ቀጣዩ ሳምንት በቤተክርስቲያን ምን ተብሎ ይጠራል? ለምን?
2. ገብርኄር ማለት ምን ማለት ነው?
3. ባለጠጋው ለባሮቹ ምን ሠጣቸው? 4. እነርሱስ በተሰጣቸው ምን ሠሩ?
5. ጌታቸው የሠጣቸውን ሲቆጣራቸው ምን አሉት?

**ይቆየን።**